# <u>የመደመርን ጽንሰ ሀሳብ</u> በጥንታዊት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሊቃውንት አባቶች እይታ ለመዳሰስ ጳጉሜ 2ሺ 10 ዓ/ም በኢትዮጵያ ኢማባሲ አዳራሽ ዋሽንግተን ዲሲ በተደረገው ጉባዔ ከቀሲስ አስተርአየ የቀረበ ።

**ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ**
**nigatuasteraye@gmail.com**

**ከራሴ ጀምሮ ከ50 ዘመን ዕድሜ በላይ ያለን ኢትዮጵያውያን** በየደረጃችን በየአቅማችንና በየእድሜያችን ከምዕራቡም ከምሥራቁም ዓለም በተቀበልነው እውቀት ሀሳባችንን፣ ቃላችንንና አቋማችንን እየቀያየርን፣ አባቶቻችን ኢትዮጵያን የገነቡባትን የኅብረነት እሴቶች እያፈረስን በግልም በጋራም በምናቀርበው ንግግር የኢትዮጵያን ህብረተ ሰብ **ከባለአገርነቱ ከባለደምነቱ** ከ**ባለአምጣነቱ** ጋራ በማጋጨት ግራ ስናገባ ኖረናልና ንስሀ እየገባን ይቅርታ እንድንጠይቅ ።

**ከእኛ ዕድሜ ማለትም ከ50 ዕድሜ ዝቅ ያላችሁ ወንድሞቻችንም ከኛ በወረሳችሁት** ጠማማ መንገድ የእርስ በርስ መበሻሸቅ ፖለቲካ ራስን አብልጦና አግዝፎ ለማሳየት በተወለዳችሁባቸው ጎጦች መሽጋችሁ በምታደርጉት የመበሻሸቅ ውድድር፣ በገባችሁም ባልገባችሁ በማወቅም ባለማወቅም የቅድመ አያቶቻችሁን ውለታ በመርሳትና የሰሯቸውን እሴቶች በማፍረስ እስካሁን ያባከናችሁት ጊዜ ይብቃችሁ። የምንጠይቃችሁንም ይቅርታ በንጹህ ህሊና በመቀበል የቀደሙ አያቶቻችሁ ኢትዮጵያን የገነቡባቸውን እሴቶች **ባለአገርነት ፤ ባለ ደምት፤ ባለአንጣትና ባለጋራነትና** የመሳሰሉትን እሴቶች ዘመኑ ከሚጠይቀው ብልሀት ጋራ ታሪካዊት ኢትዮጵያ አገራችሁን ከቀድሞዋ እጅግ የተሻለች ለማድረግ እንድተዘጋጁ።

**ከጠቅላይ ምንስትራችን ጀምሮ በዚህ ዘመን ተወልዳችሁ** ተጠራቅሞ የወደቀባችሁን ሸክም ለማስወገድ በመታገል ላይ ያላችሁ፣ ፋኖ ቄሮ ዘርማ የመሳሰላችሁ ወጣቶች! ከኛ የወረሳችሁትን ማለትም የማይጠቅመውን ለዘመናችሁም የማይመጥነውን እያረማችሁ እናት አገራችሁን መልሳችሁ በመገንባት ወደ ቀደመ ክብሯ እንድትመልሷት፣ <u>በገጠር፣ በከተማ፣ በገዳማትና በአድባራት ከነበሩት አያቶቻችሁ</u> የተማርኳቸውን **ባለአገርነትን ፤ ባለ ደምነትን፤ ባለአንጣትንና ባለጋራነትን** የተሰማኝን ከገለጽኩባት ከመግቢያየ በኋላ አቀረብኩላችሁ።

## <u>መግቢያ</u>

ለ27 ዓመታት ሲሰበክ በኖረው መለያየት ሰውነቴ ደንዝዞ አዕምሮየ ፈዞ ባለሁበት ሁኔታ፣ ጠቅላይ ምንስቴር ዶክተር ዓቢይ **እንደመር** ካሉባት ቀን ጀምሮ ከተለያዩ ሰዎች የ<u>**እንደመር**</u>ን መስተጋባት መስማት ጀመርኩ። የህሊናየ ጠጋኝና ተስፋ ሰጭ ቢሆንልኝም፤ የብዙ ትውፊት እመቤት የሆነችው እናቴ ኢትዮጵያ ከቅኝ ግዛት ነጻ እንዲወጡ ከረዳቻቸው አገሮች በታች ምንም መመሪያ ስርአት ያልነበራት ወጣኒት (novice) ሆና ስትገለጽ በመስማቴ እጅግ በጣም አዘንኩ። ከኢትዮጵያውያን ወገኖች *"ከጥንታዊት ቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንትና ከውጭም የተማርከውን ለምትወዳት አገርህ ይጠቅማታል ብለህ የምታስብላትን በማቅረብ ለ reformation አስተዋጽኦ የማድረግ ሃላፊነት ይጠበቅብሀል"* የሚል ተደጋጋሚ ጥሪ ደረሶኝ በኢምባሲ አዳራሽ በተደረገው ጉባዔ የመካፈሉ እድል ገጥሞኝ ሁለት ጊዜ ተካፈልኩ።

በኤምባሲው አዳራሽ ወለል ከተቀመጠው ህዝብ ይጎርፉ የነበሩት ሀሳቦች፤ ኢትዮጵያን ከቀሩት አፍሪቃውያን አገሮች ለይተው ከፍ እያደረጉ ያሳዩት አቀራረብ፤ ወደ ኋላ ጠምዝዘው ኢትዮጵያ የነጻነትና የስርአት መስኮት እየተደረገች ትቀርብባቸው ከነበሩ ኮሌጆች ውስጥ መልሰው ከተቱኝ። በተሳተፍኩባቸው የትምህርት አይነቶች በማቀርባቸው የጥናት ጽሑፎች እያነጻጸርኩ እስላት ከነበረችው ታላቋ ኢትዮጵያ ጋራ አገናኙኝ።

ኢትዮጵያን ሲወጓትና ስትዋጋቸው የኖሩት ቅኝ ገዥዎች አፍሪካውያንን ድምጽ አልባ ከሆኑት የሸቀጥ ማምረቻ መሳሪወቻቸው በጥቂት የሚለዩባቸውና ከሚጋልቧቸው ፈረሶቻቸውም  እጅግ ዝቅ አርገው ይመለከቱባቸው የነበሩት ህግጋት በፊቴ ተደረደሩብኝ። በዚያ ጊዜ  ኢትዮጵያ ምን ህግ ነበራት?ኢትዮጵያውያን አባቶቻችንስ ምን ይጽፉ ነበር? የአፍሪካውያን መኩሪያና ለነጻነት ትግላቸው ምሳሌ ሆና ትጠቀስ የነበረችው ኢትዮጵያስ እምን ላይ ነበረች?የሚሉና የመሳሰሉ የሀስብ ማእበላት ሰውነቴን ሰበቁት።

በዚያ የግፍና የመከራ ዘመን ተወልደው ያደጉት እንደ ጆሞ ኬንያታ የነበሩት አፍርቃውያን ግፉና መከራው ከብዷቸው መቁነጥነጥ ሲጀምሩ፤ ከከብቶቻቸውና ከዘላን ባህላዊ ኑሯቸው እጅግ ዝቅ ያለ ማፈዘዣና ማደንዘዣ customary laws የሚባል መተዳደሪያ ቀይሰውላቸው የነበረውም ትዝ አለኝ።

አፍሪቃውያን በኢትዮጵያ ተራዳኢነት ነጻ ከወጡ በኋላ፤  ቅኝ ገዥወቻቸው የጫኗቸውን ማፈዘዣና ማደንዘዣ customary laws ከላያቸው ላይ ሲወረውሩ መነሻ የሚሆናቸው ምንም አልነበራቸውም። መነሻና እርሾ የሆናቸው በቅኝ ገዥዎች ችሮታ የተቀየሰላቸው ይኸው customary laws የሚባለው ብቻ ነበር።  ቅኝ ገዥወቻቸውን የሚከሱትም በሰባዊ መብት ጥሰት እንጅ፤ ብእር ቀርጸን፤ ቀለም በጥብጠን፤ ብራና ዳምጠን በፊደላችን በቋንቋችን የጻፍነውን ህግና ደንብ አፈራረሱብን እያሉ እንዳልነበረም አስታወስኩ።

አፍሪቃ በዚህ ዓይነት ጨለማ ዘመን በነበረችበት ጊዜ፤ ኢትዮጵያውያን ባለአገሮች አባቶቻችን በመጠቀው ልዕለ አዕምሯቸው አርቀው በማሰብ፤  በአፍሪቃውያን ልጆች የሚደርሰው በኛ ላይ እንዳይደርስብን *"የኢትዮጵያዊነትን ስነ ልቡና ሳንቀርጽባቸው፤ ወጣቶቻችንን ወደ ባእድ አገር ይማሩ ብለን መላክ፤ የፈለጋችሁትን ሙሉባቸው ብለን ባዶ ሸክላ ለቅኝ ገዥዎች መላካችን አንዘንጋ። የሚሞሉባቸውን አተላና አመድ እየዛቁ በማምጣት በህዝቡ ላይ ሲደፉት ለማጽዳት በሚሞክሩ ወገኖች ላይ ከባድ ይሆናል"* እያሉ እንዲናገሩ የተገደዱበትን ምክንያት አተኩሬ አጤንኩት።

ባለአገሮች አባቶቻችን  የፈሩት በኢትዮጵያ ላይ ደርሶ፤  ተማርን የምንል ከምሥራቅም ከምዕራብም በገለበጥነው ተቃራኒና አፍራሽ ዘይቤዎች የደመሰስነውን ህይወት፤ ያጠፋነውን ንብረት፤ ያባከነውን ዘመን ቀና ብለው ቢያዩት፤ ወደ መቃብር መልሱን የሚሉ ይመስለኛል። በዚህ ጥፋት የተሳተፍን ሁሉ ኢትዮጵያውያን *"ከታናናሾች አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ የወፍጮ*

*ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባህር መስጠም ይሻለው ነበር"* <u>ብሎ ክርስቶስ የተናገረውን በራሳችን እየፈረድን ንስሀ መግባት እንደሚያንስን ተገነዘብኩ።</u>

ዶክተር አረጋዊ በርሔ "Political History of the Tigray people's Liberation Front (1975-1991)" በሚል ርእስ ለDoctoral dissertation ባሳተሙት መጽሐፋቸው ከገጽ 246 እስከ ገጽ 300 ላይ እንደገለጹት፡-የትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት ኃይሉን በመጠቀም፡-

*"የትግራይ ህዝብ ነጻ አውጭ ግንባር በ1979 አመተ ምህረት አስተሳሰብ ለዋጭ የፕሮፓጋንዳ መርሀ ግብር ለሚመለምላቸው ቀሳውስት ዘረጋ። የማሰልጠኑ ዓላማ ቤተ ክርስቲያናን ከህዝብ ለይቶ በመምታት ስፋቷን ማጥበብና በትግሬአዊነት ላይ ብቻ የተመሰረተ ስሜት በትግራይ ተወላጆች ጭንቅላት መክተት ነው። ቤተ ክርስቲያኗ ለረዥም ዘመናት በህዝቡ አዕምሮ ላይ ስትተቀርጸው የኖረችውን ብሄራዊ የኢትዮጵያነትን ስሜት ከትግራይ ህዝብ አዕምሮ ጠራርጎ በጠባቡ ትግሬአዊነት ስሜት በመተካት የቤተ ክርስቲያኒቱን ይዘት እያጠበቡ ራሷን ቤተ ክርስቲያኒቱን መምታት ነው። የወረዳ ስልጠና የተጀመረው በጠንካራ ትግሉ የታወቀው ካዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በነገረ መለኮት ትምህርት የተመረቀው ገብረ ኪዳን ደስታ ነው። የስልጠናውም ይዘት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ጠቅላላ መዋቅራዊ አስተዳደር በትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት ባለሚሎች መተካትና በቤተ ክርስቲያኒቱ አካባቢ የትግርኛ ቋንቋ እንዲሰፍን ማድረግ ነው"*

በሚለው መርሀው፤ ባለአገሮች አባቶቻችን ለረዥም ዘመናት በኀብረተ ሰቡ አዕምሮ ላይ የቀረጿቸውን እሴቶች አፈራረሷቸው። ለ27 አመታታ ሲያሸማቅቁበት የነበረው አፍራሽ መመሪያቸው ፈርሶ፤ ኢትዮጵያን reformed (እንደገና እንገንባት) ከተባለ፤ <u>**እንደገና መገንባት የሚገባቸውን የፈረሱትን እሴቶች በቅድሚያ መረዳት የሚያስፈልግ ይመስለኛል።**</u> የፈረሱት እሴቶችም የእለት ምግቤን (ውጥንቅጥ) ለማግኘት በገጠርና በከተማ፤ በገዳማትና በአድባራት ስዞር ከሊቃውንት አባቶች የተማርኳቸውና፤ ከኀብረተሰቡ የሰማኊቸው ናቸው። አባቶቻችን እርስ በርስ ከሚግባቡበትና ከሚረዳዱበት የአተረጓጎም ጽንሰ ሀሳብ ተፈልቅቀው ወጥተው በተጣመመና በሚቃረን ትርጉም ከቀረቡት እሴቶቻችን ጥቂቶችን ብቻ ጨልፌ ከዚህ በታች ለማቅረብ እሞክራለሁ።

**1ኛ፡- ባለ አገር፤ ባለ ጋራ፤ ባለ አምጣ፤ ባለ ደም፤ ባለ ቤት፤ ክልል**

<u>**2ኛ የአርበኛነት ስርጸት ፤ መዝሙራችንና ሰንደቅ አላማችን**</u>

<u>**3ኛ፡- ኢትዮጵያዊት ቅኔ**</u>

**ሀ. ኮፌዳ፤**
**ለ. ውጥንቅጥ፤**
**ሐ. ሰምና ወርቅ፤**
**መ. ሰረዝ ፤**
**ሠ. ፈለገ ግዮን**

<u>4ኛ፡-አዳዲስ ዘዴዎችን **መደመር**</u>
**ለትጻእ እሳት፤ ዓሆሆ፤ አሸክት (ጸጎጎት)፤ ጽንኢ**

## 5ኛ፡-ማጠቃልያ

**<u>ከ፤</u> እስከ 5 ከዚህ በላይ የዘረዘርኳቸውን አንቀጾች ለማብራራት እጀምራለሁ።**

**<u>ባለ</u>** የምንላት ሁለት ፊደላት የአገናዘቢ አገባብ **<u>ቁልፍ</u>** ናት። **<u>አገር፤ ጋራ፤ ደም፤ አምጣ፤ ቤት</u>** በምንላቸው ቃላት ላይ በመውደቅ የኢትዮጵያን ህዝብ ትደምራለች። የህብረተ ሰቡን ትስስር ውህደትና አድነት እንዲጣመሩ ታደርጋለች። በዚህ ጥምረት ከተወሀደው ኢትዮጵያዊ ኅብረተሰብ ማህጸን <u>አርበኛ</u> ተጸንሶ ይወለዳል። <u>ከባለ አገር</u> በመጀመር ዝርዝራቸውን እንመልከት።

### <u>ባለ አገር</u>

ከምዕራቡና ከምሥራቁ ትምህርት ታዝሎ የገባው አባቶቻችን <u>አተላ ያሉት</u> ተቃራኒ አስተሳሰብ የኛን ጭንቅላት እስከሞላበት ዘመን ድረስ፤ ማንም ኢትዮጵያዊ ካንዲት ወረዳ አጥቢያ ወይም መንደር ቢወለድም፤ ለመላ ኢትዮጵያ <u>ባለ አገር</u> ነበር። ኢትዮጵያ ከዳር እስከዳር አገሩ ነበረች። የ<u>ባለአገር</u> ትርጉም ክብር፤ ኩራት፤ እንጅ ስድብና ኋላቀርነት አልነበረም። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ለኢትዮጵያ ሁለንተና <u>ባለ አገር እና ባለጋራ</u> ነበር።

### <u>ባለጋራ</u>

**<u>ባለ</u>** እና **<u>ጋራ</u>** የሚባሉት አገባቦች በመናበብ ወደ ቃልነት ተለውጠው ወደ ህብረተ ሰብ ሲቀርቡ፤ በክልል በጎሳ በቋንቋና በሃይማኖት የተሰነቀረውን የጎረጥ መተያየት መንፈስና ስሜ አፍርሶ፤ እርስ በርሱ የተቆራኘ። በማይበጠስ ሰንሰለት የተሳሰረና የግለኝት ተቃራኒ መሆን ማለት ነው ።

### <u>ባለ ደም</u>

**<u>ባለ ደም፡-</u>** አንተ ለኔ የደሜ ባለቤት ነህ፤ እኔ ላንተ የደምህ ባለቤት ነኝ፤ ደምህን እጋራለሁ። ደምህ ደሜ፤ ደሜም ደምህ ነው። እኔ ያላንተ አንተ ያለኔ ህይወት የለም ማለትንና **የባለ አምጣነትን** መንፈስ በህብረተ ሰቡ ውስጥ የሚያሰፍን ነው።

### <u>ባለ አምጣ</u>

**<u>ባለ አምጣ፡-</u>** ሰውነታችን ይመጋገባል ይቀባበላል ይረዳዳል ይተጋገዛል ይዋዋሳል ይወሳሰዳል። ያበደርኩሁ ያበደርከኝ፤ ያቀበልኩህ ያቀበልኝ፤ ያዋስኩህ ያዋስከኝ፤ የምመልስልህ የምትመልስልኝ፤ የምታመጣልኝ የማመጣልህ የምንጓተትበት እሴት አለን። **ባለ አምጣህ** ነኝ፤ **ባል አምጣየ** ነህ በመባባል አንዱ ባንዱ ላይ የ<u>**ባለቤት**</u>ነትን መንፈስ በእኩል እያጎላ ሰማይ ዝቅ፡ መሬት ከፍ፡ ብትል አንላቀቅም የሚያሰኝ ነበር።

### <u>ባለ ቤት</u>

**<u>ባለ ቤት፡-</u>** ቤት ሁለት ትርጉም አለው። ለመኖሪያ የሚሰራው ህንጻ ሲሆን፤ ሌላው በውስጡ የሚኖሩት ባለ ቤቶች ናቸው። ጥምረታቸውን ለመግለጽ ወንዱ ለሴቷ ባለቤቷ ነው። ባለቤቱ ትለዋለች። ሴቷም ለባሏ ባለቤት ናት። ባለቤቱ ይላታል። ቤቱ የሁለቱም በእኩልነት ንብረት ነው። ኢትዮጵያ በባለ አገር፤ በባለ ጋራ፤ በባለ ደምና በባለ አምጣ ለሚነካካ ሁሉ ቤት ናት። <u>የሁሉም መኖሪያና ማደሪያ ቤት ናት</u>። በቅጽል በምሳሌ

ተሰማምቶ፤ ዜማውን ሳይሰብር፤ በማሰሪያ ግስ ህብር ተቀምሮ፤ በሀሳብ **ሳይካለል** (በፍርቅ ጸያፍ ሳይወላግድ) የሚቀርብ አመርቂ ቅኔ **ቤት መታ** ይባላል። በኢትዮጵያ ያለው ህብረተ ሰብ እርስ በርሱ ሲጋባና ሲግባባ፤ ሲሰርግና ሲሰራረግ ቤት ሰራ። እርስ በርሱ ባለቤት ትኄኄና ይባላል።

## ክልል

**ከለለ** ማለት፡- **ቆረጠ፡ ጋረደ፡ አጠረ፡ ለየ፡ ከፈለ** ማለት ነው። (በባህርዩ ምድራዊ ቆሳቁስ የማይካፈለውን አምላክ ከፍጡራን ለመለየት ብቻ ለመግለጽ ክልል የምትለውን እንጠቀማለን) ለኢትዮጵያ ዘበኛና ቤዛ የነበረው **አርበኝነት** የሚመነጭበትን አብራክ ለማድረቅ፤ የሚጸነሰበትን ማህጸን ለማምከን በምዕራቡ ትምህርት የተመለመሉ ወገኖች ህዝቡን **አካለሉት፡ አቆራረጡት፡ ጋረዱት፡ አጠሩት፡ ለዩት፡ ከፈሉት።** ከላይ የተዘረዘሩት እሴቶች የትግራይ ነጻ አውጭ ቡድን ትርጉማቸውን ገልብጦ በወጣቱ ትውልድ እስከደፋው ድረስ፤ በሥጋና በደም ላልተቀላቀሉባቸው፤ በእለታዊ፤ ሳምንታዊና አመታውያን በዓላት የማይገናኙባቸው፤ ፤ ከነሱም ያልተረከብናቸው፤ እንደ ኬንያውያን ሱዳናውያን የመሳሰሉት ጎረቤት በመባል የሚታወቁ ዜጎች የሚኖሩባቸው **አርበኞች አባቶቻችን** ያልተዋጉላቸው አገሮች ብቻ ነበሩ። በተዘረዘሩት እሴቶች ከተቆላለፈው ህብረተ ሰብ አብራክና ማህጸን የፈለቀውን **አርበኝነትንና** በአርበኝነት ውስጥ የጠናቀሩትን እሴቶች ከዚህ በታች ለማሳየት እሞክራለሁ።

## 2ኛ የአርበኛ ጽንሰ ሀሳብ፤ መዝሙራችንና ሰንደቅ ዓላማችን

ባይኖቻቸው ጨረር ሁለንተናችንን እየቃኙ፤ በእጆቻቸው ራሳችንን እየዳሰሱ ያስተማሩን ኢትዮጵያውያን መምህሮቻችን የነገሩንን ኢትዮጵያ በፈተና በወደቀችበት ጊዜ እነ ቀኝ ጌታ ዮፍታሄ ንጉሤ እነ መላከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ እነ በላይ ዘለቀን ለመቀስቀስ የተጠቀሙትን **ያርበኝነት** ስነ ልቡና እንዴትና በምን ምሳሌ እንደገለጹት ለማስታዋስ እሞ ክራለሁ።

## አርበኝነት

ታላላቅ ሊቃውንት አበው ስለ አርበኝነት ለሚቀኙት ቅኔያቸው እንደምሳሌና መሰረት አድርገው ይጠቅሷቸው ከነበሩት አንዷን በመጽሐፈ መቃቢስ *ምዕ 2፡ ከቁ 1__13* ላይ ያለችውን፡-

*“ሊነካቸው የደፈረ የለም። ጋሻና ጦራቸውን ይዘው በመገስገስ ግሰላውን እንደ ዶሮ እያነቁ የሚገድሉ፤ ስማቸውና የአደናቸው ስልት በባቢሎንና በሞአብ የተደነቀ ነበር። እጅግ በኃይል አርበኞች ነበሩ፤ የመወደድና የመከበር **ደም ግባት** ነበራቸው፤ ይቋቋማቸው ዘንድ የቻለ የለም። ወደ ተራራወቻቸው ወጥተው አመለጡ”* የምትለውን እጠቅሳለሁ ።

ይህች አረፍተ ነገር **የአርበኝነትን** ሁለንተና አካታ መያዟ እንዳለ ሆኖ “የመወደድና የመከበር **ደም ግባት** ነበራቸው” የምትለውን ሐረግ እነ ቀኝ ጌታ ዮፍታሄና ከሳቸው በኋላ የተነሱት መምህሮቼ እንደሚከተለው ይገልጿታል። **”ነጻነት ይጠሙ የነበሩት ሁሉ እንዲወዱንና እንዲያከብሩን አድርጓቸዋል። ምሳሌነታችን እንቅፋት የሆንባቸው ቅኝ ገዥዎች ቢጠሉንም በማይክዱት ህሊናቸው እንዲያከብሩን አስገድዷቸዋል”** ። በዚህ ሐረግ **ደም**

**ግባት** የምትለው ቃል **ባለ ደም** የምትለው ቃል ቋጥራ ከያዘችው ባለአገራዊት እሴት ጋራ መጠናቀሯን አንርሳ።

ሁሉንም አዳክመውና አናጥለው ለመደምሰስ ይመቻቸው ዘንድ፡-**ደም ግባት** የተባለውን የአርበኝነትን መንፈስ ስታስተምር በኖረችው በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን ላይ የአርበኝነት ስሜት አለው ብለው ከገመቱት ከማራው ህብረተ ሰብ ጋራ ደምረው ዘመቱባቸው። ሌላውን **የአርበኝነት** ስሜት የሌለው አባቶቹ ለኢትዮጵያ ያጥንትና የደም መስዋዕትነት እንዳልገበሩ ባይተዋር አገር አልባ አደረጉት። አርበኛ የምትለው ቃል ከምን እንደሰረጸች ለመረዳት አባቶች የገለጹባትን ሰዋስው እንመልከት።

## የአርበኝነት ስርጸት

ህብረተ ሰባችን **40ኛ** የሚለውን አኀዛዊ ቃል ወደ ልሙጥነት ቀይሮ **አርበኛ** ይለዋል። ለምን እንደለወጠው ለመረዳት የሚከብድ አይደለም። በቅኝ ገዥዎች ለረዥም ዘመን ያልተገዛ ህዝብ ባንድ ወቅት የጀመረውን ነገር ጽንሰ ሀሳቡን ሳይረሳ፤ ስም አጠራሩን በረዥም ዘመን ዳህጸ ልሳን እየቀየረ ጠብቆ ለትውልድ ማቀበሉ የተረጋገጠ ነው። ለምሳሌ ኢትዮጵያን ጦቢያ፤ ነነዌ የሚለውን **ነይነይ** እያለ አጠራራቸውን በመቀየር እንደሚጠራቸው ማለት ነው። እንደዚህ ሁሉ ህዝቡ **40ኛ** የምትለውን አኀዝ ወደ ፊደለኛ አነጋገር በመለወጥ በልማዳዊ ዳህጸልሳን **አርበኛ** እንደሚላት ያብነት መምህራን ነግረውናል። የ**40ኛን** ስርጸት እንዴት እንደሚገልጿት ከዚህ በታች እንመልከት!

"ስምአኒ እንዘ እመክረከ ወእግዚአብሔር የሀሉ ምስሌከ ወኩኖሙ ለህዝብ ወለእግ ወትበትከ ቃሎሙ " (ዘጽ 18፡19) ብሎ ዮቶር ለሙሴ የሰጠውን ምክርና ጥበብ ተቀብሎ፤ እስራኤላውያንን ነጻ ለማውጣት የሙሴን መንቀሳቀስ ይጠቅሳሉ።

"ወአመ ተፈጸመ **አርባ አመት** ሐለየ በልቡ የሐውጾሙ ለአኀዊኁ (የሐዋ 7፡ 23)። ማለትም፡-40ኛው አመት በተፈጸመ ጊዜ ሙሴ ወገኖቹን ነጻ ለማውጣት አሰበ። አባቶቻችን ከዚህ በመነሳት **40** ዘመንን ሰው ቁም ነገር ለሚሰራበት እድሜው ማእከል ናት ይላሉ።

ህይወቱን በትግል ጀምሮ በንስሀ የፈጸመው ዳዊት "እመሰ በዝኃ ሰማንያ ዓም ወፈድፋዶንሰ እምእላ ጻማ ወህማም" (መዝ 89፡9) ብሎ በተናገራት ሐረግም፤ አባቶቻችን የ**አርበኛን** ጽንሰ ሀሳብ አጠናክረዋታል። ይህም ማለት፡-ሰው በዚህ ዓለም የቆይታ ዘመኑ ግፋ ቢል ሰማንያ ነው። ሰውነቱ ሳይከብደው ወገቡ ሳይያዝ ቋንጃው ሳይቀየድ አቀበት ወጥቶ ቁልቁለት ወርዶ የፈቀደውን መፈጸም የሚችለው እስከ **80** ዘመኑ ነው። የ**80** ዘመኑ ማእከል የሆነችው አፍላ ዘመን **40**ኛዋ ዕድሜ ናት። ጥንቅርነቷን እንመልከት።

አርበኛ ማለት፡- **ባ** የተባለችው ፊደል ወደ **በ** በመቀየር **አርበኛ** ያሰኛታል እንጅ **አርባኛ** (**40ኛ**) ማለት አኀዝ ነው። ነፍጠኛ የምትለውን ቅጽል የተረዳንባት **ኛ** የምትለው ፊደል

ለአኀዝ ትራስ በመሆን ወደ መግለጫ ቅጽልነት እንደተቀየረች ማለት ነው። ለምሳሌ:- ፈረስ በሚለው ላይ ኛ ስትደመር ፈረሰኛ፤ በአንድ፤ በሁለት፤ በአስር ቁጥሮች ላይ ኛ ትራስ ሆና ስትደመር ወደ ገላጭ ቅጽልነት ይለወጣሉ። እንደዚሁም ኛ በ **40** ቁጥር ላይ ትራስ ሆና በመደመር **40ን** የአኀዝነትን ትርጉም ሳታስለቅቅ ግብር ገላጭ ቅጽል ታደርጋታለች።

በሀገር ላይ ዜጋን የሚፈትን ትግል ሲከሰት፤ ወደ ትግል ሜዳ በግንባር መምጣት ያለባቸው ከ20 እስከ **60** ባለው እድሜ ክልል ያሉ ናቸው። ከ**20** እስከ **60** ዘመን ላሉትም ማእከል የሚሆነው **40**ኛ ዕድሜ ላይ ያለ ነው። **40ኛ** የሠራዊት ዕጥረት ቢገጥመው በ**40ኛ ዕድሜ** ላይ **20** በመደምር እስከ **60ኛ** ዕድሜ በመሻገር ሊመለምል ይችላል። ከራሱ እድሜ ዝቅ ካለው ዜጋ መመልመል ቢፈልግም ከ20 አመት እድሜ በታች ወዳሉት ዝቅ አይልም።

አባቶቻችን ከ20 አመት እድሜ በታች ያለ ወጣት በግንባር ቀደም ለጦርነት እንዲሰለፍ የማይገፋፉት በእሳታዊ ባህርዩ ፈጥኖ በመገስገስ በሚወስደው ርምጃ በጥንቃቄና በጥናት ተዘጋጅቶ ለመጣ ጠላት እንዳይጋለጥ ሊጠነቀቁለት እንጅ፤ በፍታውራሪ ተክለ ሐዋርያት ስለ ለጋ ወጣትነት እንደተገለጸው ፤ ከ20 እድሜ በታች ባለው ወጣት ውስጥ ያለውን ኃይል ዘንግተውት አይደለም።

የአለቃ ገ/ ዮሐንስ የቅኔ ተማሪ የነበሩት ታላቁ አባታችን ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት በአድዋው ጦርነት ጊዜ የተፈጸመውን ትዝታ ባሰፈሩበት መጽሐፋቸው ከገጽ 55 እስከ 76 ላይ እንደምናነበው፤ ከ20 እድሜ በታች ያሉ በግንባር ከሚዋጉት 40ኞች ጋራ ተቀላቅለው በመዋጋት ላይ የነበሩትን ወጣቶች፤ ታላላቅ ዘማቾች ከ40ኛው ሠራዊት ለይተው በማውጣት ወደ ቤታቸው ወደ መንደራቸው እንዲመለሱ ተቆጥተው ቢሸኟቸም እንደገና እየተደበቁ ወደ ጦርነቱ ሜዳ በመቀላቀል ታላቁን ጀብዱ እንደፈጸሙ ነግረውናል። አርባኛ ጠላቱን የተከላከለበትን ነፍጥ ኛ ን በማንተራስ ነፍጠኛ (መሳሪያ ተጠቃሚ ተታኳሽ) የሚለውን ቅጽል፤ ጽንሰ ሀሳቡን በማጣመም፤ ትርጉሙን ቀይረው ማፈሪያ፡ መዋረጃ፡ መሸማቀቂያ እና መሰዳደቢያ አድርገው በትውልዱ ጭንቅላት ላይ መቅረጻቸውንም አንርሳ።

በዚህ ስርአት የዜግነታቸውን ኃላፊነት እየተወጡ ያለፉት አርባኞች አባቶቻችን፤ ወራሪዎችን ተዋግተው በማሸነፍ ድል የተቀዳጁባቸውን መሳሪያወች፤ የተሸለሚቸውን ለምድ፤ ቀሚስና ካባ እንደ ሌሎች ቆሳቁስ በሥጋ ለወለዷቸው አላወረሱም። ለተከታታዩ ትውልድ እንድትመሰከርላቸው ያስረከቡት፤ እስከ ዓለም ፍጻሜ በምድር ላይ ለምትቆየው ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናቸው ነበር።

የብዙ ትውፊት እመቤት የሆነችው እናቴ ኢትዮጵያ ከቅኝ ግዛት ነጻ እንዲወጡ ከረዳቻቸው አገሮች በታች ምንም መመሪያ ስርአት ያልነበራት ወጣኒት (novice) ሆና ስትገለጽ በመስማቴ እጅግ በጣም ያዘንኩትም፤ የእለት ምግቤን (ውጥንቅጥ) ለማግኘት በገጠና በከተማ፤ በገዳማትና በአድባራት ስዞር ከሊቃውንት አባቶች ከተማርኳቸውና፤ ከኅብረተሰቡ ከሰማኍቸው እሴቶች ጋራ በተጨማሪ እንድትመሰከርላቸው አርበኞች

ያወረሷትን ለምዶችና ቀሚሶች በየበዓሉ እየለበሱ ካደጉት የቅኔ ተማሪወች አንዱ በመሆኔ ነው፡፡

ታሪክንና አርበኝነታችንን ከባንዲራችን ጋራ አጣምራ የያዘችውን <u>**"ደሙን ያፈሰ ና ተጠማጅ አርበኛ"**</u> የምንላትን **ብሄራዊት መዝሙር** ያዘጋጇት **አርበኝነትን** ከሊቅነት አጣምረው የባህርያቸው መግለጫ ያደረጉት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ልጆች እነ ቀኝ ጌታ ዮፍታሄ ንጉሤ እረሳህን የሚሉኝ መሰለኝ፡፡ ታሪካችንን፡ አርባኛነታችንን እና የነጻነት ምሳሌነታችንን የ ምታንጸባርቀው ሰንደቅ ዓላማችን በየእለቱ ጸሀይ ስትወጣና ስትጠልቅ ይዘመርላት የነበረችውን መዝሙር እናስታውሳት፡፡

## <u>ጸሐይ ስትወጣ ትዘመር የነበረችው</u>

"ደሙን ያፈሰሰ ልቡ የነደደ<br><u>**ባርበኝነት**</u> ታጥቆ ጠላት ያስወገደ<br>ወገኑን አገሩን ክብሩን የወደደ<br>ነጻነቱን ይዞ መልካም ተራመደ

ገናና ክብራችን <u>**ሰንደቅ ዓላማችን**</u><br>ያኮራሻል <u>**አርበኝነታችን**፡፡</u>

## <u>ጸሐይ ስትጠልቅ ትዘመር የነበረችው</u>

ተተጠማጅ <u>**አርበኛ**</u> በአገር መውደድ ፍቅር<br>ገዳይ ድል አድራጊ ደም አፍሳሽ ወታደር<br>አንችን እያሰበ ይኗዛል ሲፎክር<br>ሰንደቅ አላማችን የነጻነት አገር

ገናናው ክብራችን **ሰንደቅ አላማችን**<br>ያኮራሻል <u>**አርበኝነታችን**</u>፡፡

ኢትዮጵያ በመከራ በምትወድቅበት ወቅት፤ ኢትዮጵያውያን እርስ በርሳቸው ተዳምረው ባንዲራቸውን ባንገታቸው ቋጥረው ከቆላና ከደጋ ከገጠር ከከተማ ከያሉበት በዚህች መዝሙር አማካይነት፡-

**"ወዲያ ማዶ ሆኖ ይጣራል አንድ ሰው፤**<br>**ወዲህ ማዶ ሆኖ አንድ ሰው ወይ አለው፤**<br>**ኀበዝ ተዘጋጁ ይህ ጥሪ ለኛ ነው"** እያልን እንድንጠራራ በ**ኢትዮጵያዊት** ቅኔያቸው አስተምረውን ነበር፡፡

ተማርን የምንል ሰዎች ባእዳን ባሸኩሙን አዚም ሰንደቅ ዓላማችንን ከመዝሙራች ጋራ እንድትረሳ ዘመትንባት። በተቃራኒው ተማርን ብለው የማይረገረጉ በገጠር በከተማ በተለይ በቅርብ የማውቃቸው የዋሽንግተን ዲስ 40ኞች ራሳቸውን በግብረ ኃይል ስም አደራጅተው የበረዶው ቅዝቃዜ፤ የበጋው ግለት ሳይበግራቸው ሰንደቅ ዓላማችንን ባንገታቸው ቋጥረው፤ የቤታቸውን ወጭ ሸክም በሚስቶቻቸው ጀርባ አሸክመው፤ እርስ በርሳቸው እየተጠራሩ ለውድ አገራቸው የፈጸሙትን ተጋድሎ በዚህች ማስታወሻ ብረሳቸው የዋሽንግተን ዲሲ ጋዜጦችና የጸጥታ አስከባሪ ፖሊስ መዛግብት የሚታዘቡ ይመስለኛል።

አርበኞች አባቶቻችን ቆሳቁስ ነክ የሆኑትን ንብረቶቻቸውን በሥጋ ለወለዷቸው ልጆቻቸው ሲያወርሱ፤ ተጋድሏቸውን በመፈጸማቸው የተሸለሟቸውን ካባና ለምድ ያስረከቡት 40ኛነትንና የኢትዮጵያነትን ስሜት ለረዥም ዘመናት በህዝቡ አዕምሮ ላይ ስትተቀርጸው ለኖረችውና ወደፊትም ትቀጥላለች ብለው ለሚያምኑባት ለኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ነበር።

በዚህ ዘመን በውስጧ የተሰለፍን ሁላችን የሚጠበቅብንን ሃላፊነት ረስተን በሳንቲም መለቃቀም በመሰለፋችን ጠቅላይ ምንስተር ዶ/ዓቢይ አሁን ወደተሰየሙበት ተልእኮ ከመምጣታቸው በፊት ባንድ ወቅት፡- <u>**“ድሮ ኢትዮጵያውያን ዳዊት እየደገሙ ያንን እያወጉና እየተወያዩ ያድጋሉ። በዚያው ባደጉበት ህዝባቸውን ያገለግሉ ነበር። አሁን ግን ሳንቲም ወደ መለቃቀም ተቀይሯል”**</u> እንዲሉ ያደረጋቸው፤ በታማኝነት ተልእኳቸውን ፈጽመው ያለፉትን ሊቃውንት አበው፤ ሳንቲም በመለቃቀም ዘመናችንን በማሳለፍ ላይ ካለነው ካህነት ጋራ አነጻጽረው ወድቀን በመገኘታችን ይመስለኛል። ተልእኳቸውን በታማኝነት ፈጽመው ያለፉት ሊቃውንት አበው፤ <u>በሰንደቅ አላማችን፤ በመዝሙራችንና ባአርባኝነታችን ጥንቅር ኢትዮጵያን በደመ ፍሳችን እንድትቀረጽ ያደረጉባትን **ኢትዮጵያዊት ቅኔ** ባጭሩ ላስቃኛችሁ እሞክራለሁ።</u>

## 3ኛ፡- <u>ኢትዮጵያዊት ቅኔ፤ ኮፊዳ ፤ ውጥንቅጥ፤ ሰምና ወርቅ፤ ሰረዝ፤ ፈለገ ግዮን</u>

ብዙ ዓይነት ያላት የቅኔ ትምህርታችን ከላይ በተዘረዘሩት ስሞች ኢትዮጵያዊነትን የምታጠናቅር ናት ። ከብዙ አይነቶቿ **ሰምናወርቅ** እና **ሰረዝ** የሚባሉትን የቅኔ አይነቶች ብቻ በምሳሌነት እጠቅሳለሁ። **ሰምናወርቅን** እና **ሰረዝ**ን በቦታው ለማምጣት እዚህ ላይ ገትቼ፤ ከቅኔያችን ስለማይነጠሉት፤ <u>ኢትዮጵያዊነትን ከሱስነት ወደ ነፍስነት እያመጠቁ በሁለንተናችን ስለ ቀረጹት ስለ **ኮፊዳችንና ውጥንቅጣችን** አጭር ማብራሪያ መስጠት እፈልጋለሁ።</u>

**ኮፊዳ** ከሰሌን ወይም ከቄጠማ የምንሰራት ከየመንደሩ እየዞርን በመለመን የምንሰበሰበውን ምግብ ለመያዝ የምታገለግል ዕቃ ናት። ከህብረተ ሰቡ የምንሰበስበው ልዩ ልዩ ምግብ ወደ **ኮፊዳ** ሲገባ ስሙን ለወጥን **ውጥንቅጥ** እንለዋለን። ቅኔያችን፡- ኮፎዳችንን <u>**ሰም**</u> ኢትዮጵያን <u>**ወርቅ**</u> ታደርጋለች። ከህዝቡ የምንሰበስበውን **ውጥንቅጥ** ህዝብ ገላጭ

ሰም፤ ምግቡን ሰብስባ የምትይዘውን ኮፌዳችን ሰም በመሆን ኢትዮጵያን ወርቅ እያደረች ትገልጣለች። ልዩ ልዩ ምግባችንን (ውጥንቅጥ) ቀላቅላ የያዘችው ኮፌዳችን እንዳትቀደድ እንጠነቀቃለን። ኮፌዳችን ብትቀደድ **ውጥንቅጣችን እንደ** ሚፈስብን፤ የኢትዮጵያ ድንበር ቢገሰስም እኛነታችን ይበተናል እያልን እንማራለን። የቅኔ ትምህርታችን ከኮፌዳችንና ከውጥንቅጣችን ትጸነሳለች።

## <u>ውጥንቅጥ</u>

ከላይ እንዳልኩት ከህብረተ ሰቡ የምንለምነውን **<u>ውጥንቅጥ</u> <u>ሰም</u>** ህብረተ ሰቡን **ወርቅ** እያደረገን ኢትዮጵያዊነትን እንገልጽበታለን። ለባህርያችን መግለጫ በማድረግም በሁለት መንገድ ቃሉን ሰንጠቀን እንጠቀምበታለን። **<u>ውጥን</u>** እና **<u>ቅጥ</u>** ብለን በመለያየት **<u>ውጥን</u>** ን ለ**<u>ቅጥ</u>** ገላጭ ቅጽል በማድረግ እንዳይጎብጥና እንዳይወላገድ ሆኖ የተወጠነ የተጀመረ (embryo) ማለት እንደሆነ እንርዳበታለን። ከመካከል **<u>ን</u>** ን በመሰረዝ ስንከፍለው ወጥን ቅጽል፤ ቅጥን ባለቤት በማድረግ **<u>ቀጥ ያለ</u>** አቋም ያለው የማይወላውል ማለት ይሆናል ብለውም ነግረውናል። የቅኔ ምሥጢርን ለሚያመነዥከው ጭንቅላት ኃይልና ብርታት እንዲሆነው ጥርሳችን የሚያመነዥከውን ውጥንቅጥ ቅጽል በማድረግ ለሌላ ነገርም እንጠቀመበታለን። ተዘበራርቆና **<u>ተዝጎርጉሮ</u>** ለመፍታት የሚያስቸግረንን ነገር **<u>ውጥንቅጥ</u>** በሚለው ቅጽል እንገልጸዋለን።

**"ነብር ዝጉርጉርነቱ ኢትዮጵያዊ መልኩን ይቀይራልን?"** (13፡23) እየተባለ ሲጠቀስ የምንሰማውንም አባቶቻችን እንዴት እንደሚገልጹት እንፈትሸው። ኤርምያስ ኢትዮጵያዊ መልካችን ከማይቀየረው ከነብር ዝጉርጉነት ጋራ አነጻጽሮ በጥያቄ የተናገረው፤ <u>ነጻነቱን ተገፎ ሰባዊ ክብሩን ተዘርፎ እመቀእመቃት በወደቀበት ወቅት ጎትታ ካወጣቸው ገመድ ጋራ በማነጻጸር ነው።</u> ኢትዮጵያዊው ኤርምያስን ከተወረረበት ጉድጓድ ጎትቶ አቤሜሌክ ያወጣባትን ይህች ገመድ ባላገሮች መምህሮቻችን ለወርቃማዋ አርበኛነታች መግለጫ ሰም እያደረጉ አስተምረውናል።

ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ ኤርምያስን ከገባበት ጉድጓድ በማውጣቱ **"በእኔ ስለታመንክ በምትፈራቸው ሰዎች እጅ አልሰጥህም። አድንሀለሁ። ነፍስህም እንደምርኮ ትሆናለች እንጅ አትወድቅም"** (38፡13 እንደተባለው፤ ኢትዮጵያውያንም "ለወራሪወች አሳልፋ የማትሰጥ፤ በወራሪወች እጅ ከመውደቅ የምታድን ፈጣሪን ከማመን የምትፈልቅ እምነት ነበረቻቸው። ከማትቀየረው ከነብር ዝጉርጉርነት ጋር ወርቅ ሆና የተነጻጸረችው ኢትዮጵያዊት መልክ በዓለም አቀፍ **"የመወደድና የመከበር ደም ግባት"** ያጎናጸፉችን አርበኝነታችን ናት ይሏታል።

## <u>ሰምና ወርቅ</u>

**<u>ሰም</u>** በ**<u>ቀላጭነት</u>** ባህርይዋ ለወርቁ ቅርጽና ይዘት ትለቃለች እንጅ ከወርቁ ጋራ አብራ አትዘልቅም። አንዳንድ ጊዜ እንድትቀርብ የሚያስገድድ አጋጣሚ ሲከሰትም ምሳሌ ዘየሀጽጽ ይሉታል። በወርቅና በሰም መካከል ዕሪና (equilibrium) ስለሌለ የህብረተ ሰብ መግለጫ ሆና አታገለግልም። እኔ ወርቅነኝ እያለ በህዝብ ፊት ቆሞ የሚናገር ራሱን አቅላጭ፤ ሌላውን

ቀላጭ፤ ወይም አንዱን እሳት ሌላውን ጭድ ማድረግ **ፍርቅ** ጸያፍ፤ ማለትም በአዳኝ አውሬና በታዳኝ እንስሳ መካከል ባለው ፍቅር እንደሚለካ መምህራን አስተምረውናል። ይዘቷ ከሰምና ወርቅ  በመስፋት የኢትዮጵያውነታችንን **<u>በድርብርብ</u>** መንፈስ ስለምትገልጸው ሰለ ሌላዋ ቅኔያችን ስለ ሰረዝ እገልጻለሁ።

## <u>ሰረዝ</u>

**ሰረዝ** የምትባለው የቅኔ ዓይነት እንደ ቀይ ሽንኩርት ድርብርብ ናት። ብዙ ወርቆችንና ብዙ ሰሞችን ደራርባ ስለምትይዝ ከመደበኛው ሰምና ወርቅ ቅኔ በይዘቷ ትሰፋለች። የተደራረቡት ሰሞችና ወርቆች  በዕሪና (equilibrium)  ህብር እያደረገች በቅጽሎች እና በማሰሪያ ግሶች የምታስተባብር በተለይም **ከደም፤ ካገር**፤  **ከአምጣና ከቤት** ጋር **<u>ባለ</u>** እንደ እንደምንላት አገባብ  <u>እየደመረች የምታጠነቅረን የውበታችን ደም ግባት መግለጫ ናት።</u> እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ባባቱ ከሁለት ጎን፤ በናቱ ከሁለት ጎን ቢያንስ ከአራት ድርብርብ ቤተ ሰቦች በተሸከመው **<u>ደም ግባት</u>** ሁሉንም አጣምሮ **<u>ኅብር</u>** የሚያደርግ ነው። ከዚህ ጋራ ለማትነጥፈው ቅኔያችን ሰፋድል ሆና ስለተማርንባት ስለ  **ፈለገ ግዮን**  (**ዓባይ**)  ባጭሩ ማስታወስ እፈልጋለሁ።

## <u>ፈለገ ግዮን  (ዓባይ)</u>

ለቅኔያችን አፍ መፍቻ  አድርገን የምንጠቀማትን ዓባይን፤  ከኮፌዳችን እና ከውጥንቅጣችን ጋራ የማትለይ የምሥጢር ሙዳይ እንላታን።  ስለ ዓባይ ስንቀኝ ኢትዮጵያን ነፍስ ያላት የኃያላን እናት እናደርጋታለን። አባይ የምትነጭባትን ግሸንን የኢትዮጵያ ልብ እናደርጋታለን። ከግሼ የምትፈልቀው የዓባይ ምንጭ የምታስገብራቸው አፍላጋት፤ በእናት ኢትዮጵያ መላ አካል የሚረጨውን ደም እንገልጽበታለን። ተፈጥሮ  እጓለ ማውታ ላደረጋቸው በሩቅ ላሉት ዓረባውያን ሙስሊሞችም የእንጀራ እናታቸው ናት እያሉ **<u>ባላአገሮች</u>** መምህሮቻችን አስተምረውናል።

**ባለገሮች** አባቶቻችን በነገሩን አዕናቁ እሴቶቻችን ላይ “ከባእድ ከሰማኌቸው ብዙ አስደናቂ ዕሴቶች አንድ ነገር አልጨምርም” ብየ የገባሁትን ቃል እንዳፈርስ ከላይ የጠቀስኳት የዓረባውያን ሙስሊሞች ታሪክ እንዳላልፋት ስላስገደደችኝ ይቅርታ እየጠይቅሁ፤ ከዚህ በታች ልጠቅሳት እወዳለሁ።

ለአረባውያን ሙስሊሞች ለደመ ነፍሳቸው ዋስትና ከሆነችው ዓባይ ላይ ኢትዮጵያዊት ቅኔያችን ተጨማሪ የነጻነታቸው ፋና እንደሆችላቸው አባቶቻችን ብቻ ሳይሆኑ  ብዙ ባእዳን ሊቃውንት መስክረውታል።  ከብዙ መስክሮች አንዱ  Haggai Erlich የተባሉ ናቸው።

Haggai Erlich በአባይ ተፋሰስ አካባቢ ስላሉት አገሮች The cross and the river በሚል ርእስ ባከናወኑት ጥናታዊ መጽሀፍ   ገጽ 23 ላይ “Many prominent Arabs of his time and of the late pre-Islamic period (including **<u>the famous poet, ‘Antara il bn Rabiba</u>**) were of Ethiopian desent” ማለትም፡-በዘመኑ ብዙ ዓረባውያን ታዋቂ ሰዎች ነበሩ። የታወቀ አንታራ የሚባል ኢትዮጵያዊ  የቅኔ ሰው ነበር። ነቢዩ መሀመድ በራሳቸው ወገኖች ይሳደዱ የነበሩትን ወገኖቻቸውን “Ethiopia is a land of righteousness where

God will give you relief from what you are suffering" ገጽ 24 "ብለው ወደ ኢትዮጵያ የሸኟቸው በዚያ ዘመን ባካባቢያቸው ይኖር የነበረው Antara የተባለው ተአዋቂ ዝነኛ ኢትዮጵያዊ የቅኔ ሰው አስተምሯቸዋል ይላሉ።

በ1994 የነበረው የናጀሪያው መሪ ፕሬዝደንትም ከሊንተን ለሙስሊሞቹ ያደረጉትን ቸርነት ጠቅሰው ባደረጉት ንግግር Clinton is like the king of Ethiopia in the dawn of Islam to whom the prophet himself sent his followers to find shelter" ገጽ 25 ብለዋል። እኒህ ናይጀርያዊ ፈጥረው የተናገሩት አይደለም። የካቲት 11 1994 Awatan al-Arabi በሚል ርእስ ከተዘጋጀ አገኘሁት ብለው እኛ ባላገሮች እያልን የምንንቃቸው በጨለማው ዘመን የነበሩት የኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ለሰባዊ ነጻነት ከሚቀኙት የቅኔ መዘከር ያገኙት ነበር።

Haggai Erlich "over the centuries the Ethiopian model of a righteous and legal other continued to resurface whenever Ethiopia was placed on the agenda"25 ብለው የተናገሯት የምትታለፍ አይደለችም። ማለትም፡- ኢትዮጵያ በምትታወስበት ታሪካዊ መድረክ የውይይት መነሻና መድረሻ ሆና ስትጠቀስ ትኖራለች። የደራሲው አባባል በባለአገርነት የምንፈርጃቸው አባቶች የሰሩትን ለመመስከር ላፈርንባቸው አሸማቃቂ ሲሆንብን፤ <u>ኢትዮጵያን reformed ለመድረግ ለተዘጋጀው ለቀጣዩ ትውልድ ስታንጸባርቅ የምትኖር የክብርና የልእልና ዘውድ ናት።</u>

በኢትዮጵያዊት ቅኔያችን ከግሼ የምትፈልቀው የአባይ ምንጭ የምታስገብራቸውን አፍላጋት፤ በእናት ኢትዮጵያ መላ አካል ለሚረጨው ደም ሰም አድርገን እንገልጽበታለን። ከአርበኞች የምትመነጨው ሰባዊ ክብርና ልዕልና ተፈጥሮ እጓለ ማውታ ላደረጋቸው በሩቅ ላሉት ዓረባውያን ሙስሊሞችም የእንጀራ እናታቸውና የነጻነታቸው ፋና እንደሆችላቸው በዓለም እየተነገረ ነው።

ባለመታደላችን እኛ ከ50 አመት በላይ ያለን ኢትዮጵያውያን ባላአገርነት ኋለ ቀርነት ነው በማለት ብናፍርባትም፤ "በዓለም ሁሉ በማናቸውም ስፍራ በሚሰበክበት እርሷ ያደረገችው ለእርሷ መታሰቢያ እንዲሆን ይነገራል" (ማቴ 26፡13) ብሎ ጌታችን እንደተናገረላት፤ ለ27 አመታት የተሰቃየው ትውልድ <u>ኢትዮጵያ አገራቸውን አርበኞች አያቶቻቸው</u> <u>ከ**ፈለገ ግዮን** ጋራ አጣምረው ሲያመነጬት **የኖሩት የአርበኝነት መዓዛ፤** ውድ የሆነው ሽቶ የታሸገባት **የአልባስጥሮስ ቢልቃጥ** እንደሚደርጓት አልጠራጠርም።</u> ከዚህ ቀጥየ **ባላገሮች** እያልን የምንንቃቸው አባቶቻችን አዳዲስ ዘዴዎችን <u>**በመደመር**</u> የሰሩትን ታሪክ አሳጥሬ ማስታወስ እሞክራለሁ።

## <u>**4ኛ**፡-አዳዲስ ዘዲዎችን **መደመር**</u>

### <u>ለትጻእ እሳት፤ ዓሆ፤ አሸክት (ጸጎጎት)፤ ጽንኢ</u>

ከመግቢያየ ላይ እንዳልኩት አገራችንን ከገባችበት ማጥ ለማውጣት ጠቅላይ ምንስቴር ዶክተር ዓቢይ ይዘውት የመጡት መፈክር (እንደመር) ለኢትዮጵያ አዲስ አይደለም። ከዚህ ቀደምም የነበሩ አባቶች ከገቡበት መከራ የወጡት፤ በጥበብና በማስተዋል እርስ በርሳቸው በመደማመርና በነበሩት ጠቃሚ እሴቶች ላይ አዳዲስ ጠቃሚ እሴቶችን በመደመር ነው። ስንደምርም ሆነ ስንደማመር የቀደሙ አባቶቻችን እንዳደረጉት በጥበብ፤ በማስተዋልና በጥንቃቄ እንድናደርገው "ወንደመር ምስለ እለ ይድኅኑ" ለመዳን ከሚፈልጉ እና ተስፋ ካላቸው ጋራ እንደመር" እያሉ በተለያዩ መንገዶች ነግረውናል።

"አሻሮ ይዘህ ቆሎ ወደ ያዘ ተጠጋ" ይሉን ነበር። ይም ማለት፡- አሻሮ በመያዝ ጥራት ያለው ነገር ሳትደምረው እንዳያመልጥህ፤ የጠራውን ቆሎ ለማግኘት ያልጠራውን አሻሮ ይዘህ ቅረብ፤ ቆሎውን ከያዝህ በኋላ አሻሮውን ጣለው ። አሻሮ የሚያስፈልገው የጠራ ነገር ለማግኘት እንጅ ባለህ አሻሮ ላይ ሌላ አሻሮ ለመደመር አይደለም። ሁሉም አይጠቅምምና።

ቃውንት አበው እነ መላከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬም *"የኢትዮጵያዊነትን ስነ ልቡና ሳንቀርጽባቸው፤ ወጣቶቻችንን ወደ ባእድ አገር ይማሩ ብለን መላክ፤ የፈለጋችሁትን ሙሉባቸው ብለን ባዶ ሸክላ ለቅኝ ገዥዎች መላካችን አንዘንጋ። የሚሞሉባቸውን **አተላና አመድ** እየዛቁ በማምጣት በህዝቡ ላይ ሲደፉት ለማጽዳት በሚሞክሩ ወገኖች ላይ ከባድ ይሆናል"* እያሉ ይመክሩ ነበር። ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ይህን ያሉበት በቂ ምክንያት ነበራቸው።

ዶ/ ር አረጋዊ ስለ ትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት እኩይ ተልእኮ በገለጹበት መጽሐፍ፡-

*"የትግራይ ህዝብ ነጻ አውጭ ግንባር በ1979 አመተ ምህረት የዘረጋውን እንዳወጣ ያለ እንደነገሩን አስተሳሰብ ለዋጭ የፕሮፓጋንዳ መርሀ ግብር አዘጋጅቶ ቀሳውስትን ሳይቀር እየመለመሉ ማስልጠንን ነው። ቤተ ክርስቲያናን ከህዝብ ለይቶ በመምታት ስፋቷን ማጥበብና በትግሬአዊነት ላይ ብቻ የተመሰረተ ስሜት በትግራይ ተወላጆች ጭንቅላት መክተትን ነው። ቤተ ክርስቲያኗ ለረዥም ዘመናት በህዝቡ አዕምሮ ላይ ስትተቀርጸው የኖረችውን ብሄራዊ የኢትዮጵያነትን ስሜት ከትግራይ ህዝብ አዕምሮ ጠራርጎ በጠባቡ ትግሬአዊነት ስሜት በመተካት የቤተ ክርስቲያኒቱን ይዘት እያጠበቡ ራሷን ቤተ ክርስቲያኒቱን መምታት ነው"*

ብለው የዘረጉት እና የመሳሰሉት ክፉ ነገሮች ኢትዮጵያን የማይወዱ በጭንቅላታችን እንዳይቀረጹብን ነበር። አባቶቻችን ኢትዮጵያን የተለየች ያደረጓት ባልደመረቻቸው ነገሮች ብቻ አይደለም። በየዘመኑ የገጠሟቸውን መከራ የተሻገሩት ትናንሽ የሚመስሉ ነገሮች ሁሉ ጠቃሚ ነገሮች በደመሯቸው እሴቶች ነው።

ደብረ ሊባኖስ ገዳም ይኖሩ የነበሩት የሰቆጣው ተወላጅ ዘለቱት ልሳኑ በመባል ይጠሩ የነበሩት የኔታ ፍስሀ ከዚህ የሚከተለውን ነግረውናል። (በነገራችን ላይ በጣሊያን ጊዜ የቦምብ ፍንጣሪ ምላሳቸው ተመቶ ሲናገሩ ይቸገሩ ስለነበር ዘልቱት (ተብታባው) የሚለው ቅጽል ተሰጣቸው)

ከጣሊያን ጋራ ሲፋለሙ ህይወታቸው ባለፈው በመምህር ገብረ ኢየሱስ ስም በተመሰረተው ትርጌሜ ት/ቤት በነበርኩበት ጊዜ፤ በደብረ ሊባኖስ የነበሩት የተለያዩ ጉባዔያት መምህራን በየሳምንቱ ዓርብ የሚሳተፉበት ጉባዔ የኔታ ፍስሀ ነበራቸው። የኔታ አንዳርጌ እና የኔታ አምዴ የሚባሉትን ዓይነ ስውራን የቅኔ መምህራንን እየመራሁ በመሄድ በገጠመኝ እድል ከላይ የተዘረዘሩትን እሴቶች ከደመራ ስርወ አመጣጥ ጋራ አያይዘው እንዲህ እያሉ ሲተርኩት ሰምቻለሁ።

የደመራ በዓል እስከ አጼ ገላውዴወስ ዘመን ይታወሰ የነበረው የመስቀል በዓል እየተባለ እንጅ አሁን በምናየው ስርአት በታጀበ አልነበረም። የሰፋውና የገዘፈው በዘመኑ የነበሩ ሰዎች <u>የገጠማቸውን ችግር ለመፍታት **በደመሯቸው አዳዲስ ክስተቶች ነው።**</u>

በግራኝ መሀመድ የተከሰተው ተስፋፊነት ያስከተለው ክስተት ብዙውን ህዝብ እንደ ዛሬው ከየመንደሩና ከየቤቱ አፈናቀለው። በርዳታ ስም የመጡት ፖርቱጋሎች <u>በአድዋና በመቀሌ</u> ሰፈሩ። ኢትዮጵያን ለዘላቂ ኖሯቸው ተመኟት። የህዝቡን መዳከም በመጠቀም በቆይታቸው ዘመን ለፖርቱጋል መንግሥታቸው ቅኝ ግዛት ኢትዮጵያን የማዘጋጀት ተንኮል በአድዋና በመቀሌ ህዝብ መካከል ዘረጉ። <u>ትግራይን ከመላ ኢትዮጵያ ገነጥለው በቅኝ ግዛት ለመቆጣጠር መሳሪያ ሊሆኑላቸው የሚችሉትን መልምለው በህዝቡ መካከል የመለያየትን መንፈስ አሰራጩ።</u>

አልፈው ተርፈውም የአድዋንና የመቀሌን ህዝብ ኢትዮጵያውያንን **ቁንጫወች** እያሉ በንቀት መሳደብ ጀመሩ። ኢትዮጵያንም ፖርቱጋሎችን ደም መጣጭ <u>**ትኋኖች**</u> ናችሁ ከአገራችን ውጡልን ይሏቸው ጀመር። ቅራኔው እየከረረ ሄዶ ኢትዮጵያውያን በተለመደው የመስቀል አከባበር ላይ አዲስ ዘዴ ፈጥረው **በመደመር** ነጻነታቸውን ተቀዳጁ።

ፖርቱጋሎች **ቁንጫ** እያሉ በመስደብ ሳይወሰኑ “ከዳር እስከዳር ያለው ኢትዮጵያዊ ለፖርቱጋል መንግሥት እየገበረ ነው። ከመላ ኢትዮጵያውያን ተለይታችሁ ብቻችሁን <u>**ተቆርጣችሁ ቀራችሁ**</u>” እያሉ በአድዋና በመቀሌ ያሉትን ኢትዮጵያውያን መስበክ ጀመሩ። ጥቂት ከሀድያን ካህናትን አሳምነው በህዝብ ላይ ተጽእኗቸውን አከበዱ።

ከካህናቱ መካከል ፖርቱጋሎቹ የቀየሱት ተንኮል ለትግራይ የማያዛልቅና ለጠቅላላዋ ኢትዮጵያ አደጋ መሆኑን ፈጥነው የተረዱ ካህናት፤ በጎንደር በወሎና በጎጃም ካሉት ካህናት ጋራ በመላላክ ፖርቱጋሎች “ከመላ ኢትዮጵያውያን ተለይታችሁ ብቻችሁን ተቆርጣችሁ የቀራችሁ እናንተ ብቻ ናችሁ” እያሉ ለመቀሌና ለአደዋ ህዝብ የሚሰብኩት ውሸት እንደሆነና፤ በቀረው ኢትዮጵያ ክፍል ለፖርቱጋል መንግሥት መገበር ይቅርና ስለ ፖርቱጋል መንግሥት ቅኝ ገዥነት የተሰማ ነገር እንደሌለ ተረዱ።

በዚያ ዓመት ያገጣጠመውን አመታዊ የመስቀል በዓል ለማክበር በሚደረገው ዝግጅት ከሰቆጣ ወደ መቀሌ ለሄደ አንድ የቅኔ ሊቅ አንዲት ዘዴ ተከሰተችለት። ይህች ዘዴ የመስቀሉን በዓል ለማጀብ ከየቤቱ ትጫር የነበረችው የችቦ መብራት ነበረች።

በመስቀሉ በዓል ለሚቀኘው ቅኔ ሰም ሲፈልግ "ለትጻዕ እሳት እምቤተ አቤሜሌክ፥ ከመ ትብላእ አብያተ ሴኬም፡ ወትሜሎም። ወለእመ አኮ እሳት ትጻእ እምቤተ ሴኬም ወትሜሎም ከመ ትብላዕ ቤተ አቤሜሌክ" ተብሎ በመጽሐፈ መሳፍንት ምዕ ፱ ከቁጥር ፳ ላይ የተመዘገበው ትዝ አለው። ይህም ማለት፡-"ከአቤሜሌክ ቤት የተጫረች እሳት የሴኬምንና የትሜሎምን ቤት ትብላ" ይህችን ንባብ እንደ ምሳሌ በመጠቀም በአድዋና በመቀሌ ያለውን ህብረተ ሰብ ፖርቱጋሎች ካሰሩበት ሰንሰለት ለማላቀቅ ተስማሚ ዘዴ ሆና ታየቻቸው።

እንደ እነ ቀኝ ጌታ ዮፍታሄ ብሩህ ጭንቅላት የበራቸው እኒህ ታማኝ አርበኛ ካህን ይህን ንባብ ወደ ራሳቸው ህብረተ ሰብ በማምጣት **"ከየቤታችን እየተጫረች የምትወጣ የዘንድሮው የመስቀል በዓል እሳት፥ በእርዳታ ስም መጥተው የወረሩንን ፖርቹጋሎችን ቤት ትብላ፥ በዚህ መንገድ በፖርቱጋሎች ላይ የምንወስደው እርማጃ በፈጣሪ ዘንድ ትቀባይነት ሳይኖረው ቀርቶ ረድኤቱን ከነፈገንም በፖርቹጋሎች ሥር ለዘላለም ተጠቅተን ከመኖርና ለልጆቻችንም የተገዥነትን ውርስ ከማውረስ ይሕች ከየቤታችን የጫርናት እሳት እኛኑ ትብላን"** በሚል ሀሳብ ከወሎና ከጎንደር ያለውን ህዝቡን አጠራርተው በማስማማት አንድ ላይ ደምረው ለነጻነቱ እንዲነሳ አደረጉ።

በነገራችን ላይ ኤርምያስን ከወደቀበት ጉድጓድ ያወጣችውን ገመድ፤ ኢትዮጵያን ከፖርቱጋሎች ነጻ ካወጣቻት የችቦ መብራት ጋራ እያነጻጸሩ መምህራን መዝረፋቸውን አስታውሳለሁ።

የኔታ ፍስሐ ሲናገሩ እንደሰማሁት፡- የመስቀሉ በዓል በምትከበርበት ሌሊት "ዓኾ ዓኾኋይ ሆይ ሆያዬ ንጎናይ በርሆ" እያሉ የፖርቱጋሎችን ቤት በማቃጠል ፖርቱጋሎችን አጠቋቸው። ከዚያ በኋላ በአድዋ የነበሩ ኢትዮጵያውያን "ዓኾ ዓኾኋይ ሆይ ሆያዬ ንጎናይ በርሆ" እያሉ በያመቱ ያስታውሱታል። ይህም ማለት "እናንተ ተቆርጣችሁ የቀራችሁ" እያሉ ፖርቱጋሎች ይዘልፏቸው ስለነበረ፥ "እኛ በመቀሌና በአድዋ ያለን ኢትዮጵያውያን የተቆረጣችሁ እየተባልን በራሳችን አገር ስንሰደብ አንኖርም፥ ዛሬ በዚህ ችቦ የነጻነት ብርሃን በራለን" ማለት ነው።

ፖርቱጋሎች የአድዋንና የመቀሌን ህዝብ እንደ መሳሪያ በመጠቀም ጠቅላላዋን ኢትዮጵያን ከፋፍለው ቅኝ ግዛታቸው ለማድረግ ቆርጠው ያቀዱትን ለማክሸፍ የችቦ መብራት የተጠቀሙ ሊቃውንት ካህናት **የመጣበቅ** ባሕርይ ያላትን **አሸክት** (**ጸጎጎት**) የምትባለውን ሐረግ በራሳቸው ላይ በማሰር ጸንቶ አንድ ላይ ለመቆም መልእክት ማስተላለፊያ አድርገው ተጠቅመውባታል።

<u>መስከረም ፲፮ ጽንኢ</u> በመባል በትግራይ የምትታወሰው ይህች ታሪካዊት ቅርስ፤ የፖርቱጋሎችን ከፋፋይ እኩይ ተግባር፤ ወያኔዎች በዘመናችን ከፈጸሙት ከፋፋይ እኩይ ተግባር ጋራ እያነጻጸረች በዚያ ዘመን የነበሩት አባቶች የኢትዮጵያን አንድነት አጸንተው ለመጠበቅ የከፈሉትን መስዋዕትነት ታመለክታለች። ዛሬ የመቀሌና የአድዋ ወጣት ከመላው ኢትዮጵያ ህብረተ ስብ ጋራ በመጣበቅ **"ዓኾ ዓኾኋይ ሆይ ሆያዬ ንጎናይ በርሆ"** እያለ የከደቀደሙ አባቶቹ በፖርቱጋሎች ላያ ያደረገውን እንዲደግመው የታሪከ ግዴታ ወድቆበታል። ለወደፊቱ የሚጠቅም መርሆ ለመቅረጽ የተሰየመው አካልም፤ ከዚህ በላይ የጠቀስኳቸውን አገር በቀል እሴቶች ከግምት በማስገባት የላቀ መርሆ ለኢትዮጵያ ለመቅረጽ መነሻና መድረሻ የሚሆን ሀሳብ የሚያፈልቁለት ይመስለኛል።

## <u>*መደምደሚያ*</u>

አፍሪቃ በጨለማ ዘመን በነበረችበት ጊዜ፤ ኢትዮጵያውያን አባቶች በመጠቀው ልዕለ አዕምሯቸው አርቀው በማሰብ በአፍሪቃውያን ልጆች የሚደርሰው በኛ ላይ እንዳይደርስብን *"የኢትዮጵያዊነትን ስነ ልቡና ሳንቀርጽባቸው፤ ወጣቶቻችንን ወደ ባእድ አገር ይማሩ ብለን መላክ፤ የፈለጋችሁትን ሙሉባቸው ብለን ባዶ ሸክላ ለቅኝ ገዥዎች መላካችን አንዘንጋ። የሚሞሉባቸውን አተላና አመድ እየዛቁ በማምጣት በህዝቡ ላይ ሲደፉት ለማጽዳት በሚሞክሩ ወገኖች ላይ ከባድ ይሆናል"*

ብለው ሲናገሩት የሰማሁት ደርሶ፤ ከጠላት በወረስናቸው ከፋፋይ ፖለቲካ አባቶች ተጨንቀውና ተጠበው የሰሯቸውን እንደ **ባለ<u>አገር፤ ባለጋራ፤ ባለደም፤ ባለአምጣ፤ ባለቤት</u>** እና ሌሎችንም ኅብር የሚያደርጉንን አዕናቁ እሴቶቻችንን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አውቀንም ሆነ ሳናውቅ የደመሰስናቸው ሁሉ እንደጋና በመቃኘት ለመጠቀም በንስሀና በጸጸት መንፈስ መዘጋጀት አለብን።

ተንኮለኞች መምህራን የአርበኛ የነፍጠኛ ልጆች አይደለንም በማለት አባቶቻቸው ለኢትዮጵያ አገራቸው የከፈሉትን ዋጋ እንዲክዱና አባቶቻቸው ባላወረሷቸው በሰው አገር እንደሚኖሩ አርገው እራሳቸውን እንዲያቀርቡ አደረጓቸው። ከቀረው ህዝብና ከምድሪቱ ጋራ ያላቸውን ትስስር እንዲበጣጥሱና ራሳቸውንም ለኢትዮጵያ አገራቸው ባይታወር ወፍ ዘራሾች እንዲያደርጉ የተዘመተባቸው ደባ መሆኑን ሊረዱ ይገባቸዋል።

የቀደሙ አባቶቻችን ምንም ቢሳሳቱና የሚወቀሱባቸው ስህተቶች ቢኖሩ፤ በ27 አመት የኛ ትውልድ በተለይም ወያኔወች የፈጸሙትን ያህል ግፍና በደል አልፈጸሙም። የሚወቀሱበትና የሚከሰሱበት ምንም ስህተት አልነበራቸውም ማለት አይደለም። ሰውነታቸውን ከዶ ፍጹማን መላእክት ማድረግም ስህተት ነው። ከፉብን ብንልም ከኖህ እና ከአብራህም የከፉ አልነበሩም። ኖህ በልጆቹ ፊት እርቃኑን በስካር የወደቀ፤ ከስካሩ ሲነቃ ከመጸጸት ይልቅ **"ኩን ገብረ ወነባሬ ለእሁከ"** ባሎ በልጆቹ መካከል የገዥነትንና የተገዥነት ስርአት ያወጀ ነው።

አብርሃም ባንድ ወቅት የአምላኩን ታዳጊነት የረሳ። ዋሽቶም ሳራን በውሽቱ እንድትተባበረው የደረገ ነፍሰ ገዳይ አረመኔ ከደረገው ሰው ተሽሎ ባለመገኘቱ የተከሰሰና ያፈረ ነው። ኖህም አብርሃም በዘመናቸው ከነበረው ኀብረተሰብ ተሽለው፤ ትውልድ ተሻጋሪ ስራ ስለ ሰሩ እንጅ ፍጹማን አልነበሩም።

ኖህና አብርሃም የተሳሳቱትን ያህል ተሳስተው ይሆናል፤ እንደወያኔወች ጥፍር አልነቀሉም። አሁን የምንሰማውንና እየተገለጠ የምናየውንና የምንሰማውን ወገን በወገኑ ላይ ሊያደርገው ሊያስበው ይቅርና በቅኝ ግዛት የነበሩ ሁሉ ገዥወቻችን ፈጸሙብን ብለው ሲናገሩ ሲናገሩ አልሰማንም። ተጽፎም አላነበብኩም።

ለሰባዊ ባህርይ ኖህና አብርሃምም ተስማሚ ምሳሌወች ናቸው። የማንኛውም ህብረተ ሰብ ትውልድ ካላበደ በቀር፡- የቀደሙ አባቶቹ ከሰሩት በጎ ተግባር የተሻለ ለማድረግ እንጅ የቀደሙ አባቶቹን እየረገመ የሰሩትን ደጋግ ነገሮች የሚያፈርስ ትውልድ የለም። ሊኖርም አይገባም። ከዓለም ታሪክ እንደተማርነው The Founding Fathers እየተባሉ እነ George Washington, John Adams, Thomas Jefferson, James Madison, Alexander Hamilton, እና እነ Benjamin Franklin የሚደነቁት በሰሩት ጠቃሚ ነገር እንጅ ፍጹማን መላእክት ነበሩ ማለት አይደለም።

እኛ ኢትዮጵያንም በአርበኝነትና በነፍጠኛነት ስነ ልቡናቸው ኢትዮጵያን ከውጭ ወራሪ ጠብቀው፤ በክልል፤ በጎሳ፤ በጎጥ፤ በመንደር ከመታሰር አላቀው በ<u>**ባላገር፤ በባለደም፤ በባለአምጣና በባለቤት**</u> እና በመሳሰሉት እሴቶች አስተሳስረው አንድ ያደረጉን አባቶች ልናደንቃቸው ልናከብራቸው ይገባናል።

ጠቅላይ ምንስተር ዶ/ዓቢይ አሁን ወደተሰየሙበት ተልእኮ ከመምጣታቸው በፊት ባንድ ወቅት፡- <u>**"ድሮ ኢትዮጵያውያን ዳዊት እየደገሙ ያንን እያወጉና እየተወያዩ ያድጋሉ። በዚያው ባደጉበት ህዝባቸውን ያገለግሉ ነበር። አሁን ግን ሳንቲም ወደ መለቃቀም ተቀይሯል"**</u> ያሉት ከዚህ በላይ የገለጽኳቸውን እሴቶች የከወኑትን ሊቃውንት በዚህ ዘመን ካለነው ጋራ አነጻጽረው በመታዘባቸው ይመስለኛል።

የተለያየውን ሲኖዶስ ለማስታረቅ በጣሩበት ወቅት <u>**"የጋራችንን የደመራንና የጥምቀትን እሴ አታበላሹብን"**</u> እያሉና፤ <u>**"ከጥንታዊ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ውጭ" ኢትዮጵያ ሙሉ አለመሆኗን**</u> የሰጡት ምስክርነት አባቶቻችን በሷ ውስጥ ሆነው በሰራቸው አዕናቁዕ እሴቶች ነው።

ከ50 አመት በላይ ያለን ሁላችን በደርግ ዘመን ተወልደው በኢህደግ ከፋፋይ መርሆ እየተቀረጹ ያደጉት ሁሉ <u>**ጠቅላይ ምንስቴሩን ጨምሮ፤ በእድሜ የምንልቃቸው ቢወቅሱን በበኩሌ ወቀሳው ተገቢ ነው እላለሁ።**</u> የቀደሙ አባቶቻችን በመደመር የፈጸሟቸውን ተግባራት ከኛ ባይሰሙትም፤ በደመነፍሳቸው በመቀረጹ ከ27 ዓመታት በኋላ ከገባንበት

አዘቅት እንድንወጣበት እነሆ ዛሬ በእድሜ ከምንበልጣቸው ታናናሾቻችን 40ኞች እንደገና እንዲቀርብ  ለፈቀደ አምላክ ክብር ምስጋና ይግባው።

አባቶቻችን የገጠማቸውን የመከራ ዘመን ያለፉበትን ከዚህ በላይ የገለጽኳቸውን ዘዴዎች፤ የደረስንበት ዘመን ካቀበለን ዘመናዊ ዘዴ ጋራ ደምረን፤ አገራችን ወደፊት በምትመራበት መርሆ ቢካተቱ፤ አሁን ከገባንበት ጉድጓድ ራሳችንን መንጥቀን እናወጣለን። የሚቀጥለውን ትውልድ በሚገባው ቋንቋ ብናስተምረውም ከተመሳሳይ ወጥመድ ከመውደቅ ይድናል። እናት አገራችንም  በባቶቻችን ዘመን ከነበራት ምሳሌነቷ፡ እጅግ በተሻለና በላቀ መፍለቅለቅ የምሥራቋ ኮከበጽባህ አድርገን እንደምንሰይማት ፍጹም እምነት አለኝ።

ተባርዮን የማያስቀር እግዚአብሔር ኢትዮጵያን እንደገና ይስራልን!